


# *ክህደት በደም መሬት*

*በዳዊት ወ/ጊዮርጊስ*

**<u>ሁሉም ኢትዮጵያዊ/ት ሊኖረው/ራት የሚገባ አንድ መፅሐፍ</u>**

**መ**ጽሐፉ ልዩ ልዩ የውስጥና የውጭ ኃይሎች በኢትዮጵያና ኢትዮጵያ ኃይሎች ጋራ በየምዕራፉ ትንቅንቅ ገጥመው የነበሩ ኢትዮጵያውያን ለአንድነታቸውና ለነፃነታቸው ያካሄዱት ታጋድሎ ይዘክራል:: ከውጭ ኃይሎችና ወራሪዎች እንዲሁም ከቅጥረኞቻቸውና ከሀገር በቀል ከሃዲዎች ጋር ያተደረጉት ፍልሚያዎችና ትግሎች÷ ኢትዮጵያውያን የከፈሉትን ከባድ መስዋዕትነት÷ በየምዕራፉ የታየው ጀግንነት ÷ የድልና የሽንፈቶች ፍርርቆሽ÷ የመሪዎችን ከባድ ከባድ ስህተቶችን÷ በዚህም ሳቢያ የደረሱ ፓለቲካዊና ወታደራዊ ሽንፈቶችና ውድቀቶች አመጣጥ ያሳያል:: የሀገር ህልውናና ደህንነት ቁልፍ ችግሮች --አባይ ÷ ቀይ ባህርና ኦጋዴን-- ሆነው የቆዩትን በሰፊው ይዳስሳል :: በየምዕራፉ ከገጠሙ ሽንፈቶችና ውድቀቶች ጋር የተያያዙ ክህደቶችን ያነሳል :: ለመሆኑ እነ ኢሳያስ አፈወርቂ ማንናቸው? መለስ ዜናዊስ? ÷ ሀይሌም አርአያ ÷ ሳሞራ የኑስ ቱባ ቱባ የወያኔ መሪዎች ባለፉት 35 ዓመታት የት ቦታ መቼና ምን አደረጉ? መፅሐፉ ስለነዚህ ግለሰቦች አነሳስና ማንነት የሚለው አለው:: በአንፃሩ ኤርትራዊ ኢትዮጵያውያን ለአንድነትና ለነፃነት የከፈሉት መስዋዕትነት ፤ የኤርትራ ጥያቄ ÷ የፌደሬሽን አፈታትና የችግሮቹ ታሪካዊ ሂደትን አስመልክቶ "***<u>ክህደት በደም መሬት</u>***" በሰፊ ታሪካዊ ማስረጃዎች የተደገፈ ትንታኔውንና የራሱን ምስክርነት ይስጣል::

*አፄ ዮሐንስ÷ ራስ አሉላ ÷ አፄ ሚኒሊክና ኤርትራ ÷ ኤርትራና አድዋን ታሪካዊ ማስረጃዎችን እያነሳ ያወያያል:: ቃኘው በኮሪያ÷ የኮንጎን÷ ኦጋዴንን ÷ ወልወልን÷ ዶጋሊ÷ ጉንደትና ጉራእን÷ ሃለይ ቆአቲትና ሰንአፌን የኢትዮጵያውያን አርበኝነት ትግሎች÷ የድልና የአሳዛኝ ፍጻሜዎችን ታሪክ ፤ እስከ ደርግ መንግሥት ውድቀት ድረስ የተደረጉ የታላላቅ ውጊያዎች--ዘመቻ አሉላ÷ የቀይ ኮከብ ዘመቻ÷ የቀይ ባህር ዘመቻ÷ የባህረ ነጋሽ ወዘተ..ታሪክ --እያነሳ ያስደምማል::*

*በንጉሠ ነገሥቱና በደርግ መንግስታት የነበሩ ብዙ ባለስጣኖችና የጦር መኮንኖች ስምና ግብር በሰፊው የሚገኝበት ማህደር ነው::ከሥር መሠረቱ የኢትዮጵያ ዘመናዊ መደበኛ ጦር ምስረታ ÷ ግንባታው÷ እድገቱና ውድቀቱ ብዙ ይተርካል:: የምድር÷ የአየርና የባህር ኃይሎች አመሰራረት በመጨረሻም ውድቀታቸውን ÷ በተደረጉ አያሌ ጦርነቶች የተከፈለውም መስዋዕትነት መጠን አስመልክቶ በሰፊው ቀርቧል:: ሰለ ሠራዊቱ የውጊያ ብቃት ፤ ሞራልና ያሳየው ጀግነት ብዙ ተብሎአል ፤ ተበዳይነቱንም ይናገራል:: በተለይም እውነተኛውን የቅርብ ጊዜ ታሪካችንን ዛሬ በመንበረ ሥልጣን ላይ በተቀመጡ ታሪክ አጉዳፊዎችና ከሃዲዎች በሚሞነጫጨርና "የድል አድራጊዎች የታሪክ ብወዛና ቅልበሳ" ተረት ተረት ተወናብዶ ትውልድ እንዳይረሳቸው÷ አልፎም የሕሊና እና የመታሰቢያ ሐውልት አንዲሰራላቸው ይማፀናል:: ስሜትን በእጅጉ ይቆሰቁሳል፤ ይቆጠቁጣል፤ ያስቆጫልም::*

*ፀሐፊው ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ሥፍራ ካላቸው ሰዎች አንዱ ናችው:: የሐረር ጦር አካዳሚ 2ኛ ኮርስ ምሩቅ የሆኑት ሻለቃ ዳዊት በንጉሠ ነገሥቱ ዘመን በኤርትራ ክፍለ ሃገር በጦር አሰልጣኝነት ÷ በተዋጊነት÷ በአዝማች መኮንንነት ለበርካታ ዓመታት አገልግለዋል:: ከደርግ መንግሥት ጋራ ቅራኔ ውስጥ ገብተው ሀገር ለመልቀቅ እስከተገደዱበት ወቅት ድረስም በኤርትራ ክፍለ ሀገር የበላይ ኃላፊነት ÷ በምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ÷ በእርዳታ ማስተባበርያና ማቋቋሚያ ዋና ኮሚሽነርነትና በሌሎችም ልዩ ልዩ መንግሥታዊ ኃላፊነት ቦታዎች ላይ ለበርካታ ዓመታት አገልግልዋል:: ቀደም ሲል '<u>Red Tears</u> " በሚል ርዕስ ሰለአብዮትና ረሀብ የጻፉት ሻለቃ ዳዊት አሁን ደግሞ የኢትዮጵያውያን ደም እንደ ጅረት የፈሰሰባትና ክህደት የተፈራረቀባት ኤርትራን ማዕከል አድረገው <u>ለሕዝብ ጆሮ አንግዳ የሆኑ÷ ከዚህ ቀደም ያልተነገሩና በቅጡ ያልተመዘገቡ ብዙ ጉዳዮችን በ "**ክህደት በደም መሬት**"</u> መፅሐፋቸው ይዘው ብቅ ብለዋል :: ፀሐፊው በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያን ለሁለት ከፍለው በመግዛት ላይ የሚገኙት የአዲስ አበባውና የአስመራው አገዛዞች በሚነዙት የፈጠራ ታሪክ ሳቢያ እየተፈጠረ የሚገኘውን የታሪክ መዛባት ለመከላከል በመረጃ የተደገፉ በርካታ እውነታዎችን ያቀርባሉ:: በእርግጥ በመፅሐፉ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ነጥቦችና አመለካከቶች አነጋጋሪና አከራካሪ ውይይቶችን ሊያስነሱ ይችሉ ይሆናል:: ይህም በጥልቀት ያልተፃፉ የታሪካችንን ምዕራፎች በበለጠ ለመገንዘብና ለማዳበር የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል ብለን እናምናለን:: "ማን ያውራ የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ" ነውና **<u>ክህደት በደም መሬት</u>** ብዙ ብዙ ታላላቅ ሀገራዊ ቁምነገሮችና የአያሌ ኢትዮጵያውያን ሕያው የጀግንነት ገድልና መስዋዕትነት ከታሪክ ማስረጃዎችና ከፀሐፊው የግል ገጠመኞች ጋር ተጣቅሰውና ተጣምረው የቀረቡበት ምንባብ ነው:: ትውልድ ሊያመልጠው የማይገባ መጽሐፍ:: **ክህደት በደም መሬትን ያንብቡት:: በቅርብ ቀናት ገበያ ላይ ይውላል::***

***የገጽ ብዛት፡-470 ፡ ዋጋው $30 ÷ አሳታሚ፡- ኤዞፕ አሳታሚና አከፋፋይ÷*** **ORDER ENQUIRES CAN BE SENT TO : AESOP PUBLISHERS & DISTRIBUTORS.** 43 TOWN & COUNTRY DRIVE SUITE #119, PBM-230, FREDERICKSBURG, VA 22405. USA. TEL: (202) 386-3037. **E-MAIL: <u>AESOPPUBLISHERS@AOL.COM</u>** . NUMBER OF PAGES: 470, PRICE: $30. SHIPPING AND HANDLINGFOR US AND CANADA ADD $2. SHIPPING AND HANDLING FOR EUROPE AND ELSEWHERE ADD $4. WRITE YOUR CHECK OR MONEY ORDER PAYABLE TO <u>AESOP</u>.